# ★ ዴሞክራሲያ ★

*************************************************************

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*

*************************************************************

ቅፅ 35 ልዩ ዕትም

መስከረም 2002 ዓ. ም.

## የህወሓት/ኢሕአዴግ ምርጫ - አገር ለሽብር፣ ሕዝብ ለቅርጫ

የይስሙላ ምርጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ አይደለም። የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ምርጫ፣ የደርግ ምርጫ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ ምርጫ - አንድም ሶስትም ምርጫዎች። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ አገዛዝም ይሁን የደርግ ወይም የህወሓት/ ኢሕአዴግ አገዛዞች ሁሉም ምርጫ አከናወንን ቢሉም አንዳቸውም ቢሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለስልጣን ማብቃት አልቻሉም - ሁሉም የስልጣን ዘመናቸውን ለማስቀጠል ተጠቀሙበት እንጂ። በተለይ፣ ህወሓት/ኢሕአዴግ፣ አዲስ አበባ ለመግባት ጥቂት ኪሎ ሜትር ሲቀረው የመድበለ ፓርቲ ስርዓትን እቀበላለሁ ሲል ይውገርገር እንጂ ከሎንዶኑ የ1983 ዓ. ም. ኮንፈረንስ ጀምሮ ህዝባዊና ሃገራዊ ራዕይ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ህብረ-ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች በማግለል በራሱ ዕምነት ዙሪያ ሊሰባሰቡ የሚችሉትን ብቻ በመያዝ ነበር ያለፈውን የአስራ ስምንት ዓመት አምባገነናዊ ጉዞውን የጀመረው። ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም ጋር ተያይዞ ሕዝብ የስልጣን ምንጭ እንዲሆንና ምርጫም ነጻና ፍትሃዊ ሆኖ እንዲካሄድ በምዕራባውያን ለጋሽ አገሮች በሚደረገው ዓለማቀፋዊ ግፊት ምክንያት ህወሓት/ኢሕአዴግም ምርጫ ተብዬውን በየጊዜው ማካሄድ እንዲያካሂድ ቢገደድም፣ እስካሁንም በአስተሳሰብ የሚለዩትንና ሕዝባዊና ሃገራዊ የፖለቲካ አማራጭ ይዘው የሚቀርቡትን ወገኖች ከማግለልና ከማጥቃት በሽታው ድኖ የዴሞክራሲ አባወራ ሊሆን ግን አልበቃም። ይልቁንም ዛሬም በነፍጥ የሚያምንና የሚገዛ፣ ዛሬም የመድበለ ፓርቲ ጸርና አሜከላ ሆኖ ቀጥሏል።

ከአንድ አምባገነናዊ ሥርዓት ተላቆ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመሸጋገር የሚቻለው ከመሰረቱ የመድበለ ፓርቲ ተሳትፎና ተዋጽዖ እንደመሰረት ድንጋይ ስር ሲተክል ብቻ ነው። ስርዓተ-ምርጫ የሚዋቀርበት፣ የሁሉም ፖለቲካ ፓርቲዎች አመኔታ የሚገኝበት፣ ፓርቲዎች በሕዝብ ፊት ቀርበው ፍትሃዊ በሆነ መልክ እንዲወዳደሩ የሚያስችሉ የምርጫ ህግጋት የሚወጡበትና ብሄራዊ ስምምነት የሚፈጠርበት እውነተኛ የመሸጋገርያ ሂደት መኖር ለወቅቱ ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ መሆን ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ የዴሞክራሲ ግንባታም አስተማማኝነት እጅግ ወሳኝ ነው። ህወሓት/ኢሕአዴግ በሽግግር ወቅቱ ሳይቀር ራሱና በራሱ ፍላጎት ከኮለኮላቸው አጋሮቹ በስተቀር ሌሎች ለበርካታ ዓመታት በትግል የቆዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በሂደቱ እንዳይታከሉ በማድረግ ገና ከጅምሩ ሃቀኛ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ቦታ እንዳይኖረው አድርጓል። ለጥቆም ብሔራዊና የአካባቢ ተብለው የተካሄዱ ምርጫዎቹ ጅማሯቸውም ሆነ ፍፃሜያቸው ህወሓት/ኢሕአዴግ ከስልጣን እንዳይወርድ ለማድረግ ታስበው በስሌት በተቀመረ ስርዓተ-ምርጫ፣ በአገዛዙ ተመልምለው በተሾሙ የምርጫ ኮሚሽን አባላት፣ አድሏዊና ሕዝባዊ አመኔታ ባላገኘ የፍትህ ተቋም፣ ለአገዛዙ እንጂ ለህግ የበላይነት ባልቆመ የፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት ታጅበው

የተደመደሙ ነበሩ። በተለይ በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ ወቅት የተቃዋሚው ክፍል ከአገዛዙ ይደርስበት የነበረውን ወከባና ጫና በመቋቋም የሕዝብን የዴሞክራሲ ጥማት ለማርካት ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ ቢያደርግም መታየት ጀምሮ የነበረው የለውጥ ጭላንጭል ታድያ በህወሓት/ኢሕአዴግ ጭፍጨፋ ተመልሶ ድርግም አለ። አምባገነኑ ስርዓት ምርጫ 97ን በሽብርና በአፈና ከአጠናቀቀ በኋላ በተከታታይ "ሽብርተኝነትን ለመከላከል"፣ የተራድዖ ድርጅቶች ምዝገባ"፣ "የፓርቲዎች ምዝገባ" እና "የፕሬስ ነጻነት" የሚሉና መሰል በርካታ አፋኝ አዋጆችን አውጥቶ በፀረ-ዴሞክራሲያዊነቱ መረሸ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው አገዛዙ ከጠመንጃና ከአሸባሪ አካሄዱ ሊላቀቅ ከቶም እንዳልተቻለውና የገዢው ቡድን ግንባር ቀደም ትግል በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ ሳይሆን በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ብቻ መፍጠር ነው።

ቅጥፈት፣ ታሪክ ብረዛና ተከታታይ ጥፋቶች ዋነኛ መታወቂያዎቹና መለያዎቹ የሆኑት ህወሓት/ኢሕአዴግ ከግንቦት 1997 ዓ. ም. በፊትም ደጋፊዎቹ የሆኑትን ምዕራባውያን መንግሥታት ብቻ ክፉኛ ያጭበረበረባቸው ሁለት ብሔራዊ "ምርጫ" ተብዬ ተውኔቶች ማከናወኑ ይታወሳል። በሰኔ 1987 እና በግንቦት 1992 ዓመተ-ምህረቶች የተከናወኑት እኒሁ ምርጫዎቹ ዓለም-አቀፍ የነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ህግጋትን ያላሟሉና ያልተከተሉ በአገዛዙ ብቸኛ ተወዳዳሪነት ተከናወነው በራሱ በአገዛዙ ብቸኛ አሸናፊነት የተጠናቀቁ ናቸው። ሁሌም ማጨበርበር የማይሰለቸው አገዛዝ ባሁኑ ወቅት ደግሞ ለአራተኛውና በ2002 ዓ.ም. ሊያካሂድ ላሰበው "ምርጫ" ተብዬ ተውኔቱ በከፍተኛ ልምምድ ላይ ይገኛል። ዘጠኝ ወራት ብቻ በቀሩት በዚሁ የምርጫ ተውኔት ደራሲው፤ አዘጋጁና መሪ ተዋናዩ ራሱ ህወሓት/ኢሕአዴግ መሆኑ ገሃድ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ ተዋንያንና የተውኔቱ አዳራሽ አስተናጋጆች እንዲሁም የቲኬት ክፍል ሃላፊዎች ሁሉ በህወሓት/ኢሕአዴግ የተደለደሉና በመጨረሻው ጠቅላላ ገቢና ወጪውን አስልተው ትርፉን ወደ ህወሓት/ኢሕአዴግ ኮረጆ እንዲያስገቡ መመሪያ ለመቀበላቸው እርግጥ ነው። ከጥንስሱ እስከ ፍፃሜው አራተኛውና መጪው የህወሓት/ኢሕአዴግ "ምርጫ" ቀድመውት እንደነበሩት "ምርጫዎች" ሁሉ በህወሓት/ኢሕአዴግ ትዕዛዝ ተከናውኖና ተዳኝቶ የሚጠናቀቅ መሆኑ ያፈጠጠና ያገጠጠ ዕውነታ ነው። የዚህም ሂደት አልፋና ኦሜጋም ቀድመውት እንደነበሩት ምርጫ-መሰል ድራማዎች ሁሉ አሁንም በነፃና ፍትሓዊ የምርጫ ሂደት ሊያገኝ የማይችለውን የሕዝብ ይሁንታ በነፍጥ አስገድዶ ሥልጣን በእጁ ማቆየት የሚችልበትን ዘመን ዕውን ማድረግ ነው።

ሥርዓቱ እንኳንስ ዓለም አቀፍ የነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ሕግጋትን መሰረት ያደረገና ሰላማዊ ውድድርን አክብሮ መሳተፍና ውጤቱን በፀጋ መቀበል ይቅርና ራሱ ያወጣቸውን ሕጎች እንኳ የሚጥስና ያሻውን በጉልበት ተግባራዊ የሚያደርግ ለመሆኑ አያሌ ማረጋገጫዎች ማቅረብ ቢቻልም በተለይ በቅርቡ የግንቦት 1997 ዓ. ም. ምርጫው ወቅት በቁንጮዎቹ ቀጥተኛ ትዕዛዝ የፈጸመው ሽብርና ዕልቂት እንዲሁም የምርጫ ኮሮጆ ግልበጣን ያካተቱ ተራ የሌብነት ተግባራቱ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ጭምር እጅግ አስገርሟል፤ አስቆጥቷልም። ባለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት ህወሓት/ኢሕአዴግ በራሱ አርቃቂነትና አፅዳቂነት ተፈፃሚ ያደረገው "ሕገ-መንግሥት" ተብዬ ላይ በአንቀፅነት ያሰፈራቸውን ህጎች ሳይቀር ባፈተተው እየተረገመና ሲያሻውም እየተላለፈ ለፍላጎቱ ማስፈፀሚያና ማፈኛ መሳርያ እያያደርጋቸው ቀጥሏል። በዚህ ረገድ፣ ሃገራዊና ሕዝባዊ አደራውን በመወጣት ላይ ይገኝ የነበረው ነፃው ፕሬስ ዋነኛው ሰለባ መሆኑ ከቶውንም አይዘነጋም።

ገዥው ቡድን ስልጣን ከመቆናጠጡ በፊትም ሕዝብን መከፋፈል፣ ማቃቃርና ማጋጨትን ስራዬ ብሎ ያከነውነው የነበረ ስልቱ ነበር። በጠመንጃ ሃይል ስልጣን ከያዘ በኋላም ይህንኑ ስልቱን በከፋ መልክ በማጠናከር አስተዳድረዋለሁ የሚለውን ሕዝብ በጎሣና በሃይማኖት መከፋፈልና ማጋጨቱን ቀጥሎበታል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ጎሣን ከጎሣ ማጣላትን፤ እንዲሁም ተከባብረውና ተፋቅረው ለዘመናት ባንድነት የኖሩትን የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያንን ማቃቃርና ማጋጭትን በሰፋት ተያይዞታል። ሕዝብ ባንድነት ከቆመ ማናቸውንም ከመፈፀም የሚያግደው አለመኖሩን ከግንቦት 97ቱ ምርጫ በቂ ትምህርት የወሰደው

ይኸው ገዥ ቡድን፣ ካለፈው በላቀና በከፋ ደረጃ በጎሣና በሃይማኖት ሕዝብን በማጋጨትና በመከፋፈል መሰሪ ተግባር ላይ መሰማራቱ መጪው ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ እንዳይሆን ከወዲሁ ለመወሰኑ አንዱ ጠቋሚ ድርጊት ነው።

ባሁኑ ወቅት አገዛዙ ተቃዋሚውን ሃይል ለማዳከምና ለመከፋፈል በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን በውጭ ሀገርም ጭምር በከፍተኛ ደረጃ በመራወጥ ላይ ነው። በቅርቡ "አሸባሪነትን" ለመከላከል በሚል ሽፋን መጪውን ምርጫ የሚቆጣጠርበትና ባሸናፊነትም ሊወጣ የሚያስችለውን ቅድመ-ዝግጅት አጠናቆ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል። በራሱ ለራሱ ጠቀሜታ ያወጣውን ሕግ ተብዬ እየጠቀሰ የተቃዋሚው ፓርቲ ወገን ናቸው ብሎ በሚጠረጥራቸው ንፁሃን ኢትዮጵያውያን ላይ የአፈሳ፤ የዕመቃና የእስራት እርምጃዎች በመውሰድ ሕዝብን በማሸበር የቆየ ምግባሩ ቀጥሏል። በዚሁ በቅርቡ ባወጣው ሕጉ ላይ ተመስርቶም በሃገር ውስጥ የሚገኙትን ተቃዋሚ ድርጅቶች ማስፈራራት ብቻ ሳይሆን መሪዎቻቸውን አስሯል፤ የድርጅቶቹን ጽህፈት ቤቶች ዘግቷል፤ ሰነዶቻቸውን አውድሟል፤ አባሎቻቸውንም በገሃድ በማሳደድ ላይ ይገኛል። አገዛዙ "ሕጋዊ ዕውቅና አላቸው" ለሚላቸው እንኳ ደንታ ቢስና በማንአለብኝነት ክፉኛ የተወጠረ ለመሆኑ እኒህ ሕገ-ወጥ ድርጊቶቹ ገሃድ ምስክሮች ሲሆኑ ይባስ ብሎ  ባሁኑ ወቅት አንዱን የፖለቲካ ድርጅት ከሌላው እየነጠለ "ለድርድር" የመጋበዝና ያልፈለገውን የማግለል መሰሪ ድርጊት ላይ ተሰማርቷል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያችን የገዛ ራሱን ሕግ እንኳ በማያከብርና በሕግ የበላይነት ጨርሶ በማያምን አሸባሪ፤ ጎጠኛና ከፋፋይ አምባገነን ድርጅት መዳፍ ሥር እንደምትገኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል።

"የዋጠችው ይተናነቃታል፤ በላይ በላዩ ያጎርሳታል" እንዲሉ፤ የአምባገነኑ የህወሓት/ኢሕአዴግ ስርዓት ቁንጮዎች በተለመደው የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለሌላ አሳልፎ የመስጠት የቆየ ድብቅ ዕቅድና ዓላማ ላይ ተመርኩዘው ቀደም ሲል ጀምረውት የነበረውንና ከሁመራ እስከ ጋሙ ጎፋ ጨፍ ድንበር ያለውን ርዝመቱ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር የጎን ስፋቱ ደግሞ ከሰላሳ እስከ ስልሳ ኪሎ ሜትር የሚደርሰውን ለም መሬት ለሱዳን መንግስት በገፀ-በረከትነት ለመሸለም ተዘጋጅተዋል። በዚህ የሃገር ክህደት ተግባር የሃገሪቱን ለም መሬትና ብርቅዬ የዱር አራዊት እንዲሁም ሽንፋና ጓንግን መሰል ትላልቅ ወንዞች ማጣት ብቻ ሳይሆን ለዘመናት ባካባቢው  ይኖሩ የነበሩ ወገኖቻችን ከገዛ ቀያቸው በባዕዳን ተባረው በዱር በገደሉ እንዲንከራተቱ ግድ ሆኖባቸዋል። ከሁሉም የሚገርመው የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ይህንኑ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እየፈፀሙ የሚገኙትን ስውር ሴራና ከፍተኛ የሃገር ክህደት ተግባር ምስጢር ቢያደርጉትም ድንበርን ያህል ክቡር መሬት በሽልማት የቀረበለት የሱዳን መንግሥት ግን ጉዳዩን አደባባይ በማውጣት አጋልጧቸዋል። ኢትዮጵያችን ዛሬ የገዛ ሃገሩን ዳር ድንበር እየቆረሰ ለሌላ አሳልፎ ለሚሰጥና ለወገኑ ጨርሶ  ቀናዒ ላልሆነ፤ ብሎም አስተዳድረዋለሁ ለሚለው ሕዝብ ሳይሆን ለባዕድ ጥቅም ለቆመ አገዛዝ ያለጥርጥር ተዳርጋለች። ስለዚህም ነው ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የህወሓት/ኢሕአዴግ ስርዓት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለሕዝቧ ጥቅም የቆመ አይደለምና ከሥልጣን መወገዱ የሕዝባዊ ትግሉ ዋነኛ ዓላማና ስትራቴጂያዊ ግብ መሆን እንደሚኖርበትና ለተግባራዊነቱም የሕብረት ትግል አማራጭ የማይገኝለት መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ በአፅንዖት የሚገልፀው። ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫን በሃገራችን ተግባራዊ ለማድረግ ስንነሳ ዋነኛ ዓላማችንን ማለትም የስርዓቱን ጨርሶ መወገድ ጉዳይ ከቶውንም ቢሆን መዘንጋት አይገባም። በዚህ ጥያቄም ዙሪያ አንዳችም ብዥታ መኖር የለበትም፤ ለምን ቢሉ ዓላማው በግልጽ ያልታወቀ ትግል ጨርሶ ግቡን ሊመታ አይችልምና።

ከዚህ በተጨማሪም ተቃዋሚው ሃይል የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ እየከፈለ ባላቋረጠ ሕዝባዊ ትግል ለረጅም ዓመታት የበኩሉን አስተዋፅዖ የመክፈሉን ያህል ዛሬም እንደትናንቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነት፤ እኩልነትና አንድነት እንዲሁም ማናቸውም ዓይነት ሰብዓዊ መብቶቹ መከበር ጉዳይ ላይ ዛሬም እንደትናንቱ የፀና አቋም ሊኖረውና ሊደረግ ለሚችልም የሕብረት ትግል ጥረት የመሰባሰቢያ ነጥቦች ሊያደርጋቸው ይገባል። ሃገርና ሕዝብ የማይነጣጠሉ ናቸውና። አገር ስትጠፋ

ሕዝብም ጠፉ፤ ሕዝብ ሲጣፉ አገር። የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት መጠበቅ ከቶውንም ቢሆን ለድርድር ሊቀርብ የማይችል የመሆኑ ሉዓላዊ ዕውነታ ከምንም በላይ የተቃዋሚው ጎራ የመሰባሰቢያና የመግባቢያ ትልቁ ጉዳይ መሆኑን ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አጥብቆ ያምናል።

ባሁኑ ወቅት በማንኛውም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ አዕምሮ የሚጉላሉና አፋጣኝና ግልጽ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች፣ ባለንበት የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫን አካሂዶ የሕዝብ ይሁንታን በማግኘት ለስልጣን በሚበቃ የፖለቲካ ፓርቲ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመሸጋገር የሚያስችሉ ሁኔታዎች አሉ ወይ? ነፃና ፍትሓዊ ምርጫን አስመልክቶ ከፊታችን የተጋረጠው ዋነኛ ችግር ምንድነው? ተቃዋሚው ሃይል ባሁኑ ወቅት ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? ከተጋረጡብን ችግሮች ተላቀን የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮን ለመመስረት ምን መደረግ አለበት? የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው። <u>ዕውን ወቅታዊው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ተጨባጭ ሁኔታ ከዘጠኝ ወራት በሁዋላ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫን አካሂዶ የሕዝብ ይሁንታን አግኝቶ ለስልጣን በሚበቃ የፖለቲካ ፓርቲ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገር ያስችላልን?</u>

በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ጽኑ ዕምነት ባሁኑ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ ለነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የሚያበቁ ሁኔታዎች የሉም። ለምን ቢሉ ዛሬም እንደትናንቱ ህወሓት/ኢሕአዴግ፦

- የምርጫ ሕግን አውጪ ነው።
- የምርጫ ቦርድና፣ አስፈፃሚውን ክፍል ይመድባል፤ ይቆጣጠራል።
- የምርጫ ሕግ አስፈፃሚውን ክፍል በበላይነት ይመራል።
- የፖለቲካ ምህዳሩን ለመቆጣጠር እንዲያስችለውና በመድበለ-ፓርቲ ስም እያጭበረበረ መቀጠል እንዲያመቸው በራሱ አምሳል የፈጠራቸው፤ ባንድ ጭንቅላት የሚያስቡና ባንድ አንደበት የሚናገሩ የብቻው የሆኑ አያሌ የፖለቲካ ድርጅቶች ፈብርኳል።
- በህወሓት/ኢሕአዴግ የተፈጠሩት እኒህ ድርጅቶችም በስርዓቱ ቁንጮዎች ቀጥተኛ ትዕዛዝ የታዘዙትን ብቻ የሚፈጽሙ ናቸው።
- እኒሁ የፖለቲካ ድርጅቶች በፈጣሪያቸው የተቸራቸውንና እንዲወክሉት የተመደቡበትን የፌዴራል ክልል ሕዝብ ዛሬም እንደትናንቱ ባሻቸው ያንገላታሉ፤ ያስራሉ፤ ይገድላሉ።
- ህወሓት/ኢሕአዴግ ራሱ ለራሱ ያወጣቸውን ህጎች እየጠቀሰ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ቢሮ ይዘጋል፤ ሰነዶቻቸውን ይዘርፋል፤ ያቃጥላል።
- የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን መሪዎች ያሳድዳል፤ ያንገላታል፤ ያስፈራራል፤ በፈለገው ወቅትና ጊዜም ሰበብ አስባብ እየፈጠረ ያስራል፤ ይገድላል፤
- ሌላው ቀርቶ ስርዓቱ ህጋዊ ናቸው ለሚላቸው ተቃዋሚዎች በጣም ትንሹን ጥያቄያቸውን የመሰብሰቢያ አዳራሽን እንኳ ይነፍጋቸዋል።
- ነፃውን ፕሬስ ባብዛኛው አጥፍቷል፤ የተረፈትንም በማሳደድና በማጥፋት ላይ ነው።
- የሙያ ማህበራትን የቻለውን አፍርሶ በራሱ አምሳል እንደገና ፈጥሯል፤ ያልቻለውን ፈቃድ እየነጠቀና ምክንያት እየፈለገ እንዲሁም ሰላዮቹንና ስርጎ ገቦቹን እየላከ እንዲፈርሱ አድርጓል።
- ለብሔራዊና ዓለማቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ ሰጪ እሱ ብቻ ነው።
- በሌላም ይሁን በምርጫ ወቅት የፀጥታ ጥበቃ ክፍሉ ዋና አዛዥ ህወሓት/ኢሕአዴግ ነው፤ ያሻውን ያዛል፤ ያስፈፅማል። በይፋ የስርዓቱ ጥቅም አስጠባቂ የሆነና በጠራራ ፀሐይ ሕዝብን በጥይት የሚቆላ ቅልብ ሠራዊት የማስማራት ልዩ ስልጣንም አለው።

* ለምርጫ ወቅት ከውጭ በእርዳታ የሚመጣን ቁሳቁስና ገንዘብ ሳይቀር አከፋፋይና ደልዳይ ህወሓት/ኢሕአዴግ ነው።
* በተለይ ወጣቱ ትውልድ ላይ ያነጣጠሩ ትውልድ አምካኝ ፖሊሲዎችን ማውጣትና መተግበር ብቻ ሳይሆን የለውጥ ሃዋርያውን ትኩስ ሃይል ባስከፊው ሥርዓት በስርዓቱ ላይ እንዳያምጽ ለማድረግ በጎሣ መከፋፈልና የቻለውንም በጥቅማ ጥቅም መደለልን በሚስጥር በሰፊው ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል።
* ወጣቱን ብቻ ሳይሆን አርሶ አደሩን፣ ነጋዴውን፣ ሰራተኛውን ክፍልና በልዩ ልዩ የሙያ መስክ የዕለት ኑሮውን አሸንፎ ለማደር ደፋ ቀና የሚለውን ኢትዮጵያዊ ለሕይወቱ ማቆያ የሆኑ መሰረታዊ ጉዳዮችን መያዣ እያደረገ እንዲሁም በጥቅም እየደለለ የግድ የመጪው ምርጫ ተሳታፊ ለማድረግ ቀን ተሌት ሀገርና ሕዝብ በማመስ ተግባር ላይ ነው።

በመሆኑም ምርጫን አስመልክቶ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ ብቻ ሳይሆን አድራጊም ፈጣሪም ህወሓት/ኢሕአዴግ ብቻ ነው። ያለሥርዓቱ ትዕዛዝ ሊፈፀም የሚችል አንዳችም ጉዳይ የለም። ከፊታችን የተጋረጠው ትልቁ ጋሬጣም ይኸው ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ ወገኖች በበኩላቸው ለዓመታት ከህወሓት/ኢሕአዴግ በሚደርሱባቸው በደሎችና ግፎች ክፉኛ የተጎዱ ቢሆንም የረጅም ዘመን ፖለቲካዊ ተመክሮ ያላቸውም ሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ብቅ ያሉቱ በውስጣዊ ድርጅታዊ ቀውሶች መታመሳቸው በፀረ-ህወሓት/ኢሕአዴግ ትግሉ ላይ ራሱን የቻለና አሳዛኝ የሆነ አሉታዊ አስተዋፅዖ ማድረጉም ሊዘነጋ አይገባም። በተለይም የወቅቱ ዋነኛ የትግል መፈክር ለሆነው የሕብረት ትግል በቂና አመርቂ ምላሽ ለመስጠት አለመቻላቸው በአባሎቻቸው፣ በደጋፊዎቻቸውና በዋነኛው የሕዝባዊ ትግሉ ባለቤት በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ህጸጽ መገመት አያዳግትም። በተለይ በቅድመ-ግንቦት 1997 ዓ. ም. የምርጫ ሂደት ኢዴሃህ ራሱን አጠናክሮ ለመውጣት ከፍተኛ ጥረት ባደረገበት ወቅት የተከሰቱትን ዓይነት ማፈንገጦች ዳግመኛ ላለመድገም ከፍተኛ ጥረት ካልተደረገ በጠንካራ ህብረት አምባገነኑን ህወሓት/ኢሕአዴግን በብርቱ ለመታገል የሚደረገው ትግል ስኬታማ ሊሆን አይችልም። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለ97ቱ ምርጫ ለውድድር ከመቅረቡ በፊት ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ዕውን እንዲሆን በቅድሚያ መሟላት እንዲኖርባቸው ኢዴሃህ ለአገዛዙ ያቀረባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች በሙሉ እንዲሟሉ ሲጠይቅ፤ በሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች ስብሰብ በኩል እኩል ግፊትና ትብብር ቢደረግ ኖሮ ሊገኙ ይችሉ የነበሩ ሕዝባዊ ድሎችን መለስ ብሎ ማስታወሱ የራሱ ጉልህ ታሪካዊ ጠቀሜታ አለው። በወቅቱ በኢዴሃህ አነሳሽነት ተቃዋሚው ወገን ከህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ጋር ባደረገው ድርድር በመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም፣ በታዛቢዎች መገኘትና ሌሎችም መስኮች አግኝቷቸው የነበሩ መለስተኛ ጥቅሞች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አልነበሩም። ቢያንስ ስርዓቱን ከተለመደው ግትርነቱ ሊሰብሩትና ጥንካሬና አንድነት ካለ አምባገነኑንም ቢሆን ማስጎንበስ እንደሚቻል አመላክተው ነበር። በወቅቱ በሕብረትም ሆነ በቅንጅት ሥር የተሰባሰቡት እንዲሁም ላይሰባሰቡ የቻሉት ሌሎች ጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች ትግላቸውን ሊያስወግዱት ባለሙት በህወሓት/ኢሕአዴግ ላይ ብቻ እንዲያነጣጥር አለማድረጋቸውና ባንድ ላይ ትግላቸውን አቀነባብረው ውድድራቸውን ከስርዓቱ ጋር ብቻ ማድረግ አለመቻላቸው እጅጉን ጎድቷቸው ነበር።

በ1997ቱ ምርጫ ማግስት ስርዓቱ የምርጫውን ውጤት በይፋ ሲቀለብስና ባስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የተለመደ አፈና፤ ዕመቃና ግድያውን ሲያጧጡፍም የወቅቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና ቁርጠኝነት በመጠቀም ተቃዋሚው ወገን ትግሉን የማስቀጠል ብቃት አለማሳየቱና የአመራር ክፍተትም መከሰቱ አምባገነኑ የህወሓት/ኢሕአዴግ ስርዓት እንደገና እንዲያንሰራራ ዕድል ሰጥቶታልና ይህ ለወደፊቱ የህብረት እንቅስቃሴ ታላቅ ትምህርት ሊሆን ይገባል። የህወሓት/ኢሕአዴግን ፓርላማ በመቀላቀልና ባለመቀላቀል ጥያቄ ዙሪያ በተቃዋሚው ወገን የተከሰቱት ችግሮችም ጥለውልን ያለፉት ጠባሳዎች

በቀጣዩ የትግል ሂደት የግድ መሻር ይኖርባቸዋል። ይህም ሆኖ ግን አቅምና ችሎታ በፈቀደና የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ተቃዋሚው ሃይል በወቅቱ የበኩሉን ድርሻ ከፍሏል፤ ከአምባገነኑ ስርዓት አራማጆች ጋር ግብግብ ገጥመው ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ የድርጅት አባሎችና ሃገር ወዳዶች ጥቂቶች አይደሉምና እነዚህን የዴሞክራሲና ፍትህ ሰማዕታት ዛሬም ቢሆን ልንዘነጋቸው አይገባም።

በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ዕምነት ተቃዋሚው ሃይል ዛሬም አምባገነኑን የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ሊያስወግድ የሚያስችለውንና ካለፈው ስህተቱ ትምህርት የወሰደበትን ጠንካራ ሕብረት ፈጥሮ በተግባር በመንቀሳቀስ ላይ አይደለም። ያለጥርጥር ግን በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በቅድመ ግንቦትም ሆነ በድህረ-ግንቦት፤ 97 በቀጣይነት ሳያሰልስ ለተቃዋሚው ወገን ድጋፉንና ወገንተኝነቱን በተግባር ያረጋገጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ለአዲስ ሥርዓት ምሥረታ ካለው ቁርጠኝነትና የትግል ፍላጎቱ ጋር አለ፤ ወደፊትም ይኖራል። ለዚህ ጉልህ ምስክሩ በግንቦት 97 ዓ. ም. ምርጫ ማግስትና እስካሁንም በቀጣይነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለጠንካራ መሪ የፖለቲካ ድርጅት ከህወሓት/ኢሕአዴግ ይደርስበት የነበረውንና እየደረሰበት ያለውን እርስ በርስ የማጫረስና አንዱ ባንዱ ላይ እንዲነሳ የሚደረገውን ቅስቀሳ ተቋቁሞና አንድነቱን ጠብቆ እስከዛሬ መዝለቁ ነው። ይህም የምርጫ ወቅት ዕምቅ ሃብት ብቻ ሳይሆን ለሃገሪቱም እስከዛሬ በነፃነቷ ታፍራና ተከብራ መቆየት ታላቅ ዋስትና ሆኖ የኖረ ቋሚ ቅርስ ነው።

ተቃዋሚው ሃይል ባሁኑ ወቅት ምን ማድረግ አለበት? ለሚለው ለጣቂ ጥያቄ ምላሹ የሚመነጨው ከዚሁ የተቃዋሚው ወገን መከታና ጋሻ ከሆነው ልዩ ሃይል ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለለውጥ ካለው ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ነው። በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ፅኑ እምነት በቀጣይነት እስከዛሬ ለታየውና ለተቃዋሚው ወገን ሁሌም ጠንካራ ክንዱ ሆኖ ለቆየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምላሹ በምንም መንገድ ተሰፋ መቁረጥ ሊሆን አይገባም፤ ይልቁንም ዛሬም እንደቅድመ እና ድህረ-ግንቦት 97ቱ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታውን ያገናዘበ የጋራ ግፊት በአምባገነኑ የህወሓት/ኢሕአዴግ ስርዓት ላይ በሁሉም አቅጣጫ በቀጣይነት መጧጧፍ ይኖርበታል። በምንም ዓይነት በረፈደ ፖለቲካ፤ ያውም መዘናጋት ፖለቲካ ከተሰኘ፤ ሕዝባዊ ትግሉ ለመዘናጋት ቦታ ሊኖረው አይገባም፤ መኖርም የለበትም።

ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚደረግ ትግል የአንድ ወቅት ርብርቦሽ ሳይሆን ቀጣይ፤ መራራና ረጅም ሊሆን እንደሚችል አፅንኦት ሰጥቶ ባለመዘናጋት ዛሬም ትግሉ የሚቀጥልበትን መንገድ በተግባር ማሳየት የሕዝብ ወገን ነኝ ከሚል የፖለቲካ ድርጅት ሁሉ ይጠበቃል። ከትናንቱ ስህተት መማር እንጂ ስህተቱን ልንደግም በፍፁም ፈቃደኞችም ዝግጁም መሆን የለብንም። ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ በተለይም ህወሓት/ኢሕአዴግ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን ከማሟላት ይልቅ ሁሉንም ምርጫ ነክ ጉዳዮች በቁጥጥሩ ስር ባደረገበት ሁኔታ በነፃ ውድድር ሕዝብ ይሁንታውን የሰጠበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረት አይቻልም ስንል እጃችንን አጣጥፈንና ለአምባገነኖች አስቀድመን ተቸንፈን እንንበርከክ ማለታችን አይደለም። እንታገልልሃለን ለምንለውም ሕዝብ ተስፋ መቁረጥን ልንመክረው ከቶም መዳዳት የለብንም፤ ይልቁንም ከመከራውና ከስቃዩ ሊያወጡት የሚችሉ ዘዴዎችን ማፍለቅ የሚጠበቅብን ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም ነው። ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ የሚጠይቃቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት የሚቻለው ከራሳችን በመነጨና ባላቋረጠ የዓላማ አንድነት፣ ጽናትና የትግል ስልት ሲሆን መፍትሄያችንም እኛውና እኛ ብቻ መሆናችንን በፍፁም መሳት የለብንም። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ በመጠየቅ ላይ ያለው ታግሎ የሚያታግል፣ ለድል የሚያበቃ አመራር ሊሰጥ የሚችልና በተቃዋሚ ድርጅቶች ሕብረት ሊፈጠር የሚገባን የጋራ ግንባር በተመለከተ ነው። “ውሃን ከጥሩ፤ ነገርን ከስሩ” እንዲሉ፤ ከራሣችንም ጋር ሆነ ከምንታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ባለንበት ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ግልፅ መሆናችን ለሕብረት ትግሉ ከመነሳት አስቀድሞ ምን ነባራዊ ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ ማሳየታችን እንጂ ተቸናፊነትን አስቀድመን መቀበላችን እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል።

የህወሓት/ኢሕአዴግ ምርጫ ከዘጠኝ ወራት በሁዋላ በራሱ አወዳዳሪነትና ተወዳዳሪነት መደረጉ አይቀሬ ነውና የተቃዋሚው ጎራ፦

- የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሚገባው ስልጣን ሊያበቃው በሚችለውና ሌላ አማራጭ ለሌለው ለወቅታዊው የሕብረት ምስረታ ጥያቄ ዛሬም በቂ ተግባራዊ ምላሽ ሊሰጥ የግድ ነው።
- የህወሓት/ኢሕአዴግን ዕድሜ ለሚያራዝመውና ሁሌም ተቃዋሚውን ክፍል ለመከፋፈል ለሚያመቸው የውጭና የውስጥ ለሚባል ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን ለሚከፋፍል በታታኝ የስርዓቱ ድርጊት ሳይሸነፉ ላንድ ዓላማ ባንድ ላይ ሆኖ በመገኘት ላይ ማትኮርና የትግሉ ሜዳ ለሁሉም እኩል የሚሆንበትን መንገድ መቀየስና ይህም ዕውን እስኪሆን ተደጋጋፊ ትግል ማካሄድ ዛሬም የግድ ነው።
- በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙቱ ተቃዋሚዎች የተናጠል ሩጫዎች ትናንትም ሆነ ዛሬ ከዋናው የትግሉ ስትራቴጂያዊ ዓላማና ግብ ማለትም ህወሓት/ኢሕአዴግን ከማስወገዱ ድል ሊያደርስ እንዳልቻለ አውቆ የሕብረት ግንባር ምስረታን ዓላማው ወዳደረገ መድረክ መምጣት የግድ ነው።
- በጋራ መድረኩ የመሰባሰቢያና የሕብረት መታገያ ነጥቦች ላይ ተስማምቶ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች አውጥቶ መንቀሳቀስ ዛሬም የግድ ነው።
- በግል ሳይሆን በጋራ አምባገነኑን ሥርዓት ወደ ክብ ጠረጴዛ እንዲመጣ ሊያስገድዱ የሚያስችሉ ድርድሮችን ብቻ ማድረግ የግድ ነው።
- ዓለማቀፉን ሕብረተሰብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አጋር ለማድረግ የሚያስችሉ ማናቸውም ጥረቶች (ሰላማዊ ሰልፎች፣ የሻማ መብራቶች፣ የዲፕሎማሲ ሥራዎች፤ ወዘተ) በተናጠል ሳይሆን በጋራና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሆኑ ማድረግ ዛሬም የግድ ነው።
- ለተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የተቋቋሙና የሚቋቋሙ የተግባር ኮሚቴዎች በጋራና በሕብረት ድርጊቶቻቸውን እንዲያስተባብሩ ማድረግ የግድ ነው።
- የሙያ የፆታና የሃይማኖት ድርጅቶችን የሕዝባዊው ትግል አጋር እንዲሆኑ ማስቻልና ማቀናጀት የግድ ነው።
- የምሁራን፣ የሙያ፤ የፆታና የሲቪክ ማህበራት ወሳኝ ሚና ዛሬም በሁላችንም ዘንድ ግልፅነት ሊኖረው የግድ ነው።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ከግንቦት 6 እስከ 9፤ 2001 ዓ. ም. ባካሄደው አምስተኛው ጠቅላላ የአባላት መደበኛ ጉባዔው የኢትዮጵያን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች በጥሞና ከገመገመ በሁዋላ "የሃገራችንና የሕዝቧ መሠረታዊ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት ሥርዓቱን በተባበረ ትግል ማስወገድ ሲቻል መሆኑ ታውቆ ለህብረትና ለተቀናጀ ትግል ዝግጁ መሆንና ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ ነው" በሚል ግንዛቤ አቋም አውጥቶ ይፋ አድርጓል። ይህም አቋሙ አሁንም የጸና ነው። ስለዚህም በድርጅታችን ዕምነት ከዘጠኝ ወራት በሁዋላ በሃገራችን ውስጥ በህወሓት/ኢሕአዴግ የመሃልና የመስመር ዳኝነት ተግባራዊ ሊሆን የታሰበው ምርጫ፦

1) በገለልተኛ የምርጫ አውጭና አስፈፃሚ አካል እስካልተመራ፤
2) የምርጫውም ሕግ ዓለም-አቀፍ የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መርሆችንና ሕግጋትን እስካልተከተለና ይህንኑ እስካላሟላ፤
3) ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎችን እስካላሣተፈ፤
4) የመገናኛ ብዙሃን ዘርፎች፣ በሙሉ ነፃነት፣ ቅድመ-ምርጫና ድህረ-ምርጫ ሂደቶችን ያላንዳች ፖለቲካዊና ወታደራዊ ጣልቃ-ገብነት እንዲዘግቡ እስካልተደረገ፤

5) የፀጥታ ክፍሉ በምርጫው ሂደትም ሆነ ውጤት ምንም ተሳትፎ እንዳይኖረው እስካልተገደበና
6) ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እስካልተፈቱ ድረስ - ነፃና ፍትሓዊ ሊሆን አይችልም፤ ተቀባይነቱም በስርዓቱና በጋሻ ጃገሬዎቹ ብቻ ይሆናል ብለን እናምናለን።

ከዚህ በፊት ደግመን ደጋግመን ለማስረገጥ እንደሞከርነው ተቃዋሚው ሃይል የሙያ፤ የፆታና ሌሎች የሲቪክ ማህበራትን ያካተተና የትግሉን ዋነኛ ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳተፈ ጠንከር ያለ ግፊት በህወሓት/ኢሕአዴግ ላይ ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም። ቀደም ሲል ለዘመናት ሲደረጉና መስዋዕትነት ሲከፈልባቸው የኖሩ እንዲሁም ዛሬም ሆነ ነገ ሊደረጉ የሚችሉ ፀረ-ህወሓት/ኢሕአዴግ ትግሎች የቀጣዩ፤ የመራራውና የረጅሙ የዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምስረታ ትግል ታሪክ አካል መሆናቸው ታውቆ በጎጠኛው፣ በአሸባሪውና በአምባገነኑ ስርዓት መወገድ ላይ ከተቃዋሚው ጎራ የተቀናጀ አመራር መስጠት የሚጠበቀው ጭቆናው ይበልጥ እየበረታና ያገራችንም ሉዓላዊነትና ድንበራዊ አንድነት አጅግ አሳሳቢ ሆኖ ባለበት ባሁኑ ወቅት ነው።

በሃገሪቱ ውስጥ ከህወሓት/ኢሕአዴግ ጋር ምርጫውን አስመልክቶ በሚደረጉ ማናቸውም ድርድሮች ተደራዳሪዎች ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባው ለነፃና ፍትሓዊ ምርጫ መሟላት ለሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች መሆን አለበት። ስርዓቱ በ"ነጣጥለህ ምታውና ከፋፍለህ ግዛው" ሤራ እጅጉን የተካነ ነውና ዳግም ለመሞኘትና የህዝብን የስቃይ ዘመን ለማራዘም በጭራሽ መፈቀድ የለበትም። እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ "በህወሓት/ኢሕአዴግ ምርጫ ተብዬ ተሳትፌ በማሸነፍ ለስልጣን እበቃለሁ" የሚል አጉል ተስፋ ማሳደሩ አንድም ስርዓቱን በቅጡ አለማወቅ ሁለትም ከቅርቡ የምርጫ 97 ዓ. ም. ታሪካዊ ሂደት አለመማር ወይም ለመማር ፈቃደኛ አለመሆን ነው። የትግሉ ዋነኛ ዓላማ ለመሠረታዊ እንጂ ለጥገናዊ ለውጥ አለመሆኑን ከቁብ በማስገባት የሕዝብ አጋርነታቸውን በእስካሁኑ የትግል ሂደት በተግባር ያስመሠከሩ ተቃዋሚ ሃይሎች ትግላቸውን ከመቼውም ይበልጥ ማቀናጀት ያለባቸው ዛሬ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ በትግሉ አካሄድና አቅጣጫ እንዲሁም ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ተሳታፊ መሆኑ ወሳኝ ነው።

የህወሓት/ኢሕአዴግ አምባገነን ቡድን ባለፉት ሦስት ምርጫ ተብዬ ሂደቶቹ፣ በተለይም በቅርቡ የግንቦት 1997ቱ በነፍጥ የታገተ ምርጫ ወቅት ፣ ስልጣኑን ላለማስነካት ሲል በአረመኔነት ሕዝቡንም ሆነ የሕዝቡን ወገን በተለይም ተቃዋሚውን ሃይል ፋታ ሳይሰጥ እያሳደደ ከመጨፍጨፍ እንደማይመለስ በግልፅ አረጋግጧል። ያለበቂ ዝግጅት እንዲሁም ያልተባበረና ያልተቀነባበረ ትግል በስመ-ምርጫ ዓመት እየቆጠረ በሚመጣና ስርዓቱ አስቀድሞ ሁሉንም በጁ በደጁ በሚያደርግበት "ምርጫ" ተብዬ ሃገርን ለሽብር ሕዝብን ለቅርጫ የምንዳርግበት ሁኔታ መቆም አለበት እንላለን። ማናቸውም ትግል መስዋዕትነት ማስከፈሉ አይቀሬ ቢሆንም በኢትዮጵያችን በጠመንጃ በመግዛት ላይ የሚገኘውን የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሽቀንጥሮ ለመጣልና ለማስወገድ ብቸኛው መንገድ የተቃዋሚ ሃይሎች ሕብረት መፍጠርና የተቀናጀ ሕዝባዊ ትግል ማድረግ ብቻ ነው።

ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ሥርዓት በትግላችን ይመሠረታል!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
እናቸንፋለን!